Seattle Department of Education & Early Learning

SEATTLE PRESCHOOL PROGRAM

# የምዝገባ ጥቅል

## Seattle Preschool Program 2026 - 2027

ደረጃ 1፡- የምዝገባ ጥቅሉን ይሙሉ → ደረጃ 2፡- ሰነዶችን ይሰብስቡ → ደረጃ 3፡- ለ DEEL ወይም ለአቅራቢው ያስገቡ → ደረጃ 4፡- የምዝገባ ማረጋገጫ ይቀበሉ

## ደረጃ 1፡- የምዝገባ ጥቅሉን ይሙሉ

የሲያትል ቅድመ-ትምህርት ቤት ፕሮግራም (Seattle Preschool Program) የዜግነት ሁኔታ (citizenship)፣ ዘር፣ ጾታ፣ ጎሳ ወይም የእድገት ፍላጎት ምንም ይሁን ምን ብቁ ለሆኑ ልጆች ሁሉ ክፍት ነው። ሲያትል (Seattle) እንግዳ ተቀባይ ከተማ (welcoming City) ናት ምክንያቱም በአካታችነት (inclusion) እና በፍትሃዊነት (equity) እናምናለን። የከተማው የስራ እድል የዜግነት ሁኔታን (citizenship) አይጠይቁም እንዲሁም የኢሚግሬሽን (immigration) ሁኔታ ምንም ይሁን ምን ሁሉንም ነዋሪዎች (residents) ያገለግላሉ። እዚህ መጤዎች (Immigrants) እና ስደተኞች (refugees) መልካም አቀባበል ይደረግላቸዋል። ልጅዎን በተሻለ ሁኔታ ለማገልገል፣ እባክዎ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሱ።

| **የልጅ መረጃ** | | | |
|---|---|---|---|
| የመጠሪያ ስም:- | የአባት ስም:- | የአያት ስም:- | የትውልድ ቀን:- |
| የጾታ ማንነት:-<br>☐ ሴት ☐ ወንድ ☐ ባይነሪ ያልሆነ ወይም ሌላ ጾታዊ ማንነት ያለው ___________ | | | |
| ልጁ በቅድሚያ የተማረው ቋንቋ:- | | ቤት ውስጥ ብዙ ጊዜ የሚነገር ቋንቋ:- | |
| ይህ ልጅ በማደጎ ወይም በዘመድ ጥበቃ (የሙሉ ጊዜ በዘመድ ወይም በሌሎች ተስማሚ የሆኑ ሰዎች የልጅ እንክብካቤ) እንክብካቤ ላይ ነው?<br>☐ አዎ ☐ አይ | | | |
| በትምህርት ሰአታት፣ ልጅዎ በጤና ሁኔታ እርዳታ ያስፈልገዋል? (ማለትም አለርጂ፣ የስኳር በሽታ፣ የደም ስኳር፣ የሚጥል በሽታ፣ የዓይን/ጆሮ ጠብታዎች) አለበት? ☐ አዎ ☐ አይ<br>አዎ ከሆነ፣ እባክዎን ያብራሩ:- | | | |

| **የልጅዎ ዘር እና ብሔር ምንድን ነው? *አግባብነት ያለው ሁሉ ላይ ምልክት ያድርጉ።*** | | | |
|---|---|---|---|
| **እስያዊ** | ☐ ምስራቅ እስያዊ<br>☐ ፊሊፒኖ | ☐ ደቡብ እስያዊ<br>☐ ደቡብ ምስራቅ እስያዊ | ☐ ሌላ ወይም በይበልጥ ልዩ እስያዊ |
| **አሜሪካ ሕንዳዊ፣ የአላስካ ተወላጅ** | ☐ አሜሪካ ሕንዳዊ<br>☐ የአላስካ ተወላጅ | ☐ ማዕከላዊ ወይም ደቡብ አሜሪካ ሕንዳዊ | ☐ ሌላ ወይም በይበልጥ ልዩ አሜሪካ ሕንዳዊ/የአላስካ ተወላጅ ___________ |
| **ጥቁር፣ አፍሪካዊ፣ አፍሪካ አሜሪካዊ** | ☐ አፍሪካ አሜሪካዊ<br>☐ ካሪቢያን<br>☐ ማዕከላዊ አፍሪካዊ | ☐ ምስራቅ አፍሪካዊ<br>☐ ላቲን አሜሪካዊ<br>☐ ደቡብ አፍሪካዊ | ☐ ምዕራብ አፍሪካዊ<br>☐ ሌላ ወይም በይበልጥ ልዩ ጥቁር ___________ |
| **ሂስፓኒክ፣ ላቲኖ** | ☐ ካሪቢያን<br>☐ ማዕከላዊ አሜሪካዊ | ☐ ሜክሲኳዊ/ቺካኖ<br>☐ ደቡብ አሜሪካዊ<br>☐ ስፓኒያርድ | ☐ ሌላ ወይም በይበልጥ ልዩ ሂስፓኒክ/ላቲኖ |
| **መካከለኛው ምስራቅ ወይም ሰሜን አፍሪካዊ** | ☐ መካከለኛው ምስራቃዊ<br>☐ ሰሜን አፍሪካዊ | ☐ ሌላ ወይም በይበልጥ ልዩ መካከለኛው ምስራቃዊ/ሰሜን አፍሪካዊ | |
| **የሐዋይ ተወላጅ፣ ሌላ የፓስፊክ ደሴት ተወላጅ** | ☐ ማይክሮኔዥያን<br>☐ ሜላኔዥያን | ☐ ፖሊኔዥያን (የሐዋይ ተወላጅን ጨምሮ) | ☐ ሌላ ወይም በይበልጥ ልዩ የሐዋይ ተወላጅ/የፓስፊክ ደሴት ተወላጅ ___________ |
| **ነጭ** | ☐ ነጭ | ☐ ሌላ ወይም በይበልጥ ልዩ ነጭ ___________ | |

| ተቀዳሚ ወላጅ/አሳዳጊን የሚመለከት መረጃ | | | |
|---|---|---|---|
| የመጠሪያ ስም፦ | መካከል፦ | የአያት ስም፦ | የትውልድ ቀን፦ |
| የጾታ ማንነት፦ ☐ ሴት ☐ ወንድ ☐ ባይነሪ ያልሆነ ወይም ሌላ ጾታዊ ማንነት ያለው ____________ | | | |
| የኢሜይል አድራሻ፦ | | ከልጅ ጋር ያለ ዝምድና፦ | |
| ግንኙነት ለማድረግ የሚመርጡት ቋንቋ፦<br><br>ቤት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ተቀዳሚ ቋንቋ | የስልክ ቁጥር 1፦ ዓይነት፦ ☐ ባለ ገመድ ስልክ ☐ የስራ ☐ ሞባይል ስልክ<br>የስልክ ቁጥር 2፦ ዓይነት፦ ☐ ባለ ገመድ ስልክ ☐ የስራ ☐ ሞባይል ስልክ<br>*ሞባይል ስልክ ከሆነ፣ በአጭር የጽሑፍ መልእክት አማካይነት ወቅታዊ መረጃዎችን ልንልክልዎት እንችላለን?* ☐ አዎ ☐ የለም | | |

| የእርስዎ ዘር እና ብሔር ምንድን ነው? *አግባብነት ያለው ሁሉ ላይ ምልክት ያድርጉ።* | | | |
|---|---|---|---|
| **እስያዊ** | ☐ ምስራቅ እስያዊ<br>☐ ፊሊፒኖ | ☐ ደቡብ እስያዊ<br>☐ ደቡብ ምስራቅ እስያዊ | ☐ ሌላ ወይም በይበልጥ ልዩ እስያዊ<br>____________________ |
| **አሜሪካ ሕንዳዊ፣ የአላስካ ተወላጅ** | ☐ አሜሪካ ሕንዳዊ<br>☐ የአላስካ ተወላጅ | ☐ ማዕከላዊ ወይም ደቡብ አሜሪካ ሕንዳዊ | ☐ ሌላ ወይም በይበልጥ ልዩ አሜሪካ ሕንዳዊ/የአላስካ ተወላጅ ____________ |
| **ጥቁር፣ አፍሪካዊ፣ አፍሪካ አሜሪካዊ** | ☐ አፍሪካ አሜሪካዊ<br>☐ ካሪቢያን<br>☐ ማዕከላዊ አፍሪካዊ | ☐ ምስራቅ አፍሪካዊ<br>☐ ላቲን አሜሪካዊ<br>☐ ደቡብ አፍሪካዊ | ☐ ምዕራብ አፍሪካዊ<br>☐ ሌላ ወይም በይበልጥ ልዩ ጥቁር<br>____________________ |
| **ሂስፓኒክ፣ ላቲኖ** | ☐ ካሪቢያን<br>☐ ማዕከላዊ አሜሪካዊ | ☐ ሜክሲኳዊ/ቺካኖ<br>☐ ደቡብ አሜሪካዊ<br>☐ ስፓኒያርድ | ☐ ሌላ ወይም በይበልጥ ልዩ ሂስፓኒክ/ላቲኖ<br>____________ |
| **መካከለኛው ምስራቅ ወይም ሰሜን አፍሪካዊ** | ☐ መካከለኛው ምስራቃዊ<br>☐ ሰሜን አፍሪካዊ | ☐ ሌላ ወይም በይበልጥ ልዩ መካከለኛው ምስራቃዊ/ሰሜን አፍሪካዊ<br>____________________ | |
| **የሐዋይ ተወላጅ፣ ሌላ የፓስፊክ ደሴት ተወላጅ** | ☐ ማይክሮኔዥያን<br>☐ ሜላኔዥያን | ☐ ፖሊኔዥያን (የሐዋይ ተወላጅን ጨምሮ) | ☐ ሌላ ወይም በይበልጥ ልዩ የሐዋይ ተወላጅ/የፓስፊክ ደሴት ተወላጅ ____________ |
| **ነጭ** | ☐ ነጭ | ☐ ሌላ ወይም በይበልጥ ልዩ ነጭ ____________________ | |

| ሁለተኛ ወላጅ/አሳዳጊን የሚመለከት መረጃ (አንድ ቤተሰብ ውስጥ ከሆነና ከልጁ ጋር በደም ወይም በጋብቻ ዝምድና ካለ።) | | | |
|---|---|---|---|
| የመጠሪያ ስም፦ | መካከል፦ | የአያት ስም፦ | የትውልድ ቀን፦ |
| የጾታ ማንነት፦ ☐ ሴት ☐ ወንድ ☐ ባይነሪ ያልሆነ ወይም ሌላ ጾታዊ ማንነት ያለው ____________ | | | |
| የኢሜይል አድራሻ፦ | | ከልጅ ጋር ያለ ዝምድና፦ | |
| ግንኙነት ለማድረግ የሚመርጡት ቋንቋ፦<br><br>ቤት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ተቀዳሚ ቋንቋ | የስልክ ቁጥር 1፦ ዓይነት፦ ☐ ባለ ገመድ ስልክ ☐ የስራ ☐ ሞባይል ስልክ<br>የስልክ ቁጥር 2፦ ዓይነት፦ ☐ ባለ ገመድ ስልክ ☐ የስራ ☐ ሞባይል ስልክ<br>*ሞባይል ስልክ ከሆነ፣ በአጭር የጽሑፍ መልእክት አማካይነት ወቅታዊ መረጃዎችን ልንልክልዎት እንችላለን?* ☐ አዎ ☐ የለም | | |

| የእርስዎ ዘር እና ብሔር ምንድን ነው? *አግባብነት ያለው ሁሉ ላይ ምልክት ያድርጉ።* | | | |
|---|---|---|---|
| **እስያዊ** | ☐ ምስራቅ እስያዊ<br>☐ ፊሊፒኖ | ☐ ደቡብ እስያዊ<br>☐ ደቡብ ምስራቅ እስያዊ | ☐ ሌላ ወይም በይበልጥ ልዩ እስያዊ<br>____________________ |
| **አሜሪካ ሕንዳዊ፣ የአላስካ ተወላጅ** | ☐ አሜሪካ ሕንዳዊ<br>☐ የአላስካ ተወላጅ | ☐ ማዕከላዊ ወይም ደቡብ አሜሪካ ሕንዳዊ | ☐ ሌላ ወይም በይበልጥ ልዩ አሜሪካ ሕንዳዊ/የአላስካ ተወላጅ ____________ |
| **ጥቁር፣ አፍሪካዊ፣ አፍሪካ አሜሪካዊ** | ☐ አፍሪካ አሜሪካዊ<br>☐ ካሪቢያን<br>☐ ማዕከላዊ አፍሪካዊ | ☐ ምስራቅ አፍሪካዊ<br>☐ ላቲን አሜሪካዊ<br>☐ ደቡብ አፍሪካዊ | ☐ ምዕራብ አፍሪካዊ<br>☐ ሌላ ወይም በይበልጥ ልዩ ጥቁር<br>____________________ |
| **ሂስፓኒክ፣ ላቲኖ** | ☐ ካሪቢያን<br>☐ ማዕከላዊ አሜሪካዊ | ☐ ሜክሲኳዊ/ቺካኖ<br>☐ ደቡብ አሜሪካዊ<br>☐ ስፓኒያርድ | ☐ ሌላ ወይም በይበልጥ ልዩ ሂስፓኒክ/ላቲኖ<br>____________ |
| **መካከለኛው ምስራቅ ወይም ሰሜን አፍሪካዊ** | ☐ መካከለኛው ምስራቃዊ<br>☐ ሰሜን አፍሪካዊ | ☐ ሌላ ወይም በይበልጥ ልዩ መካከለኛው ምስራቃዊ/ሰሜን አፍሪካዊ<br>____________________ | |
| **የሐዋይ ተወላጅ፣ ሌላ የፓስፊክ ደሴት ተወላጅ** | ☐ ማይክሮኔዥያን<br>☐ ሜላኔዥያን | ☐ ፖሊኔዥያን (የሐዋይ ተወላጅን ጨምሮ) | ☐ ሌላ ወይም በይበልጥ ልዩ የሐዋይ ተወላጅ/የፓስፊክ ደሴት ተወላጅ ____________ |
| **ነጭ** | ☐ ነጭ | ☐ ሌላ ወይም በይበልጥ ልዩ ነጭ<br>____________________ | |

## የቤተሰብ መረጃ

**የቤት አድራሻ**
(ቤት አጥ ከሆኑ፣ የርስዎን የሌሊት ወቅት አድራሻ)
መንገድ:

ከተማ: ዚፕ ኮድ:

**የፖስታ መላላኪያ አድራሻ** (የተለየ ከሆነ)

መንገድ:

ከተማ: ዚፕ ኮድ:

የእርስዎ መኖሪያ ቤት የተረጋጋ ነው? በአሁኑ ጊዜ መኖሪያ ቤት አጥ ከሆኑ እና/ወይም የመኖሪያ ቤት አለመረጋጋት እያጋጠመዎት እንደሆነ ምልክት ያድርጉ። ☐ አዎ ☐ አይ

**የራስዎን ቤት ባለቤት ካልሆኑ/ የተከራዩ ካልሆነ፣ እባክዎን የሚመለከተውን ሁሉ ምልክት ያድርጉ።** <u>በአሁኑ ወቅት ልጅ አመልካቹ እና እኔ እንኖርን ያለነዉ</u>

☐ በሞቴል ውስጥ ☐ በመጠለያ ውስጥ ☐ የሽግግር መኖሪያ ቤት
☐ ከቦታ ወደ ቦታ በመዘዋወር/ የሶፋ ላይ በመቅዘፍ ☐ በምጣኔ ሃብት ችግር ምክንያት በጊዜያዊነት ከሌላ ቤተሰብ/ ሰው ጋር መኖር ☐ በቂ ያልሆነ ማመቻቸት በሌለበት መኖሪያ ውስጥ (ውሃ፣ ሙቀት፣ ኤሌክትሪክ የሌለው) ☐ መኪና፣ ፓርክ፣ የካምፕ መስክ ወይም ተመሳሳይ ቦታ
☐ ሌላ:

የእርስዎ ቤተሰብ/ ተማሪ በWA ስቴት የአድራሻ ሚስጥራዊነት ፕሮግራም ተመዝግበዋል? ☐ አዎ ☐ አይ
*መልሱ አዎ ከሆነ፣ እባክዎ በመጨረሻው ገጽ ላይ ከተዘረዘሩት የአድራሻ ሰነዶች ይልቅ እንድ የእርስዎን ACP ካርድ ቅጂ ያስገቡ*

የእርስዎን አድራሻ ከDEEL ጋር ሪፖርት ማድረግ/ ማረጋገጥን በተመለከተ ምንም አይነት የደህንነት ስጋት አለዎ? ☐ አዎ ☐ አይ

*መልሱ አዎ ከሆነ፣ የእርስዎን ለፕሮግራም ብቁ መሆን ለማረጋገጥ DEEL በቀጥታ ያገኝዎታል።*

ለDEEL የሚያስገቡት መረጃ ሚስጥራዊ ነው እና ለእርስዎ አከራይ ወይም የንብረት ሥራ አስኪያጅ አናገኝም/ አንዘግብም (ሪፖርት አናደርግም)።

**እባክዎን የእርስዎ ቅድመ ትምህርት ቤት በፊት/በኋላ እንክብካቤ የሚሰጥ ከሆነ ብቻ ይመልሱ:**

**የእርስዎ ቤተሰብ ከ6 ሰአታት የሲያትል ቅድመ ትምህርት ፕሮግራም (SPP) ውጭ እንክብካቤ በፊት/በኋላ ያስፈልገዋል?** ☐ አዎ ☐ አይ

አዎ ብለው ካመለከቱ፣ ስለ መገኘት እና ስለ መርሀ ግብሩ ከእርስዎ ቅድመ ትምህርት ቤትዎ ጋር ያረጋግጡ እና ልጅዎ ከእንክብካቤ ሰዓታት በፊት/ በኋላ እንዲመዘገብ። **SPP ለእንክብካቤ በፊት/በኋላ መቀመጫዎችን ማዘጋጀት ወይም ማቆየት አይችልም።**

**መልሱ አዎ ከሆነ፣ የእርስዎ ቤተሰብ በአሁኑ ጊዜ በልጅ እንክብካቤ ድጎማ ፕሮግራም ተመዝግቧል?**

☐ የዋሽንግተን ስቴት የስራ ግንኙነቶች (WCCC) ☐ ለህፃናት ድጎማ ከሁሉ ይልቅ ምርጥ ጅምር ☐ የልጅ እንክብካቤ ድጋፍ ፕሮግራም (CCAP)
☐ አልተመዘገበም

**SPP ማንኛቸውም ካለ፣ ምን ያህል ለትምህርት ክፍያ ዕዳ እንዳለብዎት ለመወሰን እንዲረዳ ለማወቅ፣ ከታች የተመለከተውን መረጃ ይጠቀማል።** ለትምህርት ክፍያ የሚዘጋጀው በቤተሰብ ብዛት እና ገቢ ላይ በመመስረት ተንሸራታች በሆነ ሚዛን በመጠቀም ነው።

**ወላጆችን/ አሳዳጊ ሞግዚቶችን ሁሉንም አይነት ገቢዎች ያካትቱ።** ደመወዞችን፣ ሥራ አጥነት፣ የልጅ ማሳደጊያ/ ድጋፍ፣ SSI፣ የገንዘብ ድጋፍ፣ TANF፣ ወዘተ ግምት ውስጥ ማስገባት።

**በቤቱ ውስጥ የሚኖሩ እና በወላጅ/ አሳዳጊ ሞግዚቶች ገቢ የሚደገፉ፣ እና ከወላጅ ጋር በደም፣ በጋብቻ ወይም በጉዲፈቻ የተገናኙ ሰዎችን ከዚህ በታች መዘርዝር።** በታች የተዘረዘሩት ልጆች ገቢ ይኖራቸዋል ተብሎ አይጠበቅም።

**በማደጎ ወይም በሥጋ ዝምድና እንክብካቤ ውስጥ ያሉ ልጆች** የገቢ ሰነዶችን እንዲያቀርቡ አይገደዱም ነገር ግን የዕድሜ እና የአድራሻ ማረጋገጫ ሰነዶችን ማስገባት አለባቸው።

| ከእርስዎ ጋር የሚኖሩ <u>እና</u> በቤተሰብዎ ገቢ የሚደገፉትን ሁሉንም የቤተሰብ አባላት የሆኑትን (እራስዎንም ጨምሮ) መዘርዝር | የልደት ቀን | ከልጁ ጋር ያለው ግንኙነት | የገቢ አይነት (ደሞዝ፣ ሥራ አጥነት፣ የልጅ ማሳደጊያ ድጋፍ፣ SSI፣ ወዘተ) | አመታዊ ከግብር በፊት ገቢ | ይህ ሰው ገቢ አለው? |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ☐ አዎ ☐ አይ |
| | | | | | ☐ አዎ ☐ አይ |
| | | | | | ☐ አዎ ☐ አይ |
| | | | | | ☐ አዎ ☐ አይ |
| | | | | | ☐ አዎ ☐ አይ |
| | | | | | ☐ አዎ ☐ አይ |
| | | | | | ☐ አዎ ☐ አይ |
| | | | | | ☐ አዎ ☐ አይ |
| | | | | | ☐ አዎ ☐ አይ |
| | | | | | ☐ አዎ ☐ አይ |
| **ከ SNAP የምግብ ፕሮግራም ወይም ከTANF የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራም እርዳታ እያገኙ ነው?** | | | | | ☐ አዎ ☐ አይ |

የልጁ የመጀመሪያ/የመጨረሻ ስም፦ ______________________________ የልጁ የትውልድ ቀን፦ ____________________

**<u>የሲያትል የቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤት ፕሮግራም የተሳትፎ ፈቃድ</u>**

Department of Education and Early Learning ("DEEL"፣ የመደበኛ እና የቅድመ-መደበኛ ትምህርት መምሪያ) ለልጅዎ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን አገልግሎቶች እና ድጋፎች ለመስጠት ከቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤት አገልግሎት አቅራቢዎች ("አገልግሎት አቅራቢው") ጋር በቅርበት ይሠራል። በፕሮግራሙ ውስጥ ለመሳተፍ ተሳታፊዎች በሚከተሉት መስማማት አለባቸው፦

DEEL የልጅዎን ምዝገባ፣ የትምህርት ምዘና እና ለትምህርት የመገኘት ሁኔታ ጨምሮ፣ ማንነትን የሚገልጹ የተማሪ መረጃዎችን ጥብቅ ቁጥጥር በሚደረግበት እና አስተማማኝ በሆነ የመረጃ ቋት ውስጥ ያስቀምጣል። አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን ለመስጠት እና ተማሪዎች ወደ ዲስትሪክቱ የኬ-12 (K-12) ትምህርት ፕሮግራሞች በሚሸጋገሩበት ጊዜ የትምህርት ቀጣይነትን ለማረጋገጥ ሲባል ማንነትን ሊገልጹ የሚችሉ መረጃዎች በ DEEL፣ በአገልግሎት አቅራቢው፣ በ Seattle School District No. 1 ("ዲስትሪክቱ"፣ የሲያትል የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ቁጥር 1)፣ በ Public Health- Seattle & King County ("PHSKC"፣ የሲያትል እና ኪንግ ካውንቲ የሕዝብ ጤና ጥበቃ) እና በ Washington State Department of Children, Youth and Families ("ስቴቱ"፣ የዋሽንግተን ስቴት የሕፃናት፣ ወጣቶች እና ቤተሰብ መምሪያ) መካከል ሊጋሩ ይችላሉ።

DEEL የልጅዎን የጤና፣ የትምህርት እና የዕድገት ፍላጎቶች ለማሟላት ከጤና ጋር የተያያዙ መረጃዎችን የውል ስምምነት ላላቸው አገልግሎት አቅራቢዎች ደኅንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ሊያጋራ ይችላል። በልጅዎ የመማር ሂደት ላይ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን ለመለየት የጤና ምርመራዎች ይካሄዳሉ። ከ PHSKC ከሚገኝ ስልጠና እና ድጋፍ ጋር አገልግሎት አቅራቢዎች የዓይን እና የጆሮ ምርመራዎችን ሊያካሂዱ ይችላሉ። በተጨማሪም የልጅዎን የዕድገት ሂደት ለመገምገም አገልግሎት አቅራቢዎች Ages and Stages Questionnaires (የዕድሜ እና የዕድገት ደረጃዎች መጠይቅ)ን ሊጠቀሙ ይችላሉ። መምህራን ከ PHSKC የሥርዓተ-ምግብ ባለሙያ፣ ነርስ ወይም የባሕሪ ጤና አማካሪ ጋር እንዲመካከሩ ማስቻልን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ ድጋፎችን ለተማሪዎች ለመስጠት ሲባል፣ የምርመራ ውጤቶች ለአገልግሎት አቅራቢው፣ ለ PHSKC እና ለ DEEL ሊጋሩ ይችላሉ። ለልጅዎ ተጨማሪ እርምጃዎች እንዲወሰዱ የሚመከር ከሆነ፣ አገልግሎት አቅራቢው ውጤቱን ለእርስዎ ያሳውቃል።

ምዘናዎች የተሻሉ የትምህርት አሠራሮችን ለመምህራን ለማሳወቅ፣ ለሙያዊ እድገት ድጋፍ ለመስጠት እና ፕሮግራሙን ለመገምገም ጥቅም ላይ ይውላሉ። መምህራን የልጅዎን አካላዊ፣ አእምሯዊ (Cognitive)፣ ማኅበራዊ እና ስሜታዊ ዕድገት ሊከታተሉ እና ምልከታዎቻቸውን Teaching Strategies GOLD® ("TSG"፣ የትምህርት ስትራቴጂዎች ጎልድ) የተሰኘው የኦንላይን ግምገማ መሣሪያ ላይ ሊመዘግቡ ይችላሉ። የአገልግሎት አቅራቢዎች እና DEEL ከስቴቱ ጋር በጋራ በሚጠቀሙት አካውንት አማካኝነት TSGን ማግኘት ይችላሉ፤ በተጨማሪም የ TSG ውጤቶች ለዲስትሪክቱ ይጋራሉ።

የ DEEL የቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤት ፕሮግራሞች ልጅዎን ለመዋዕለ ሕፃናት እና ከዚያ ባሻገር ላለው ትምህርት ለማዘጋጀት ይሠራሉ። ልጆች ለትምህርት ምን ያህል ውጤታማ በሆነ መንገድ እንደተዘጋጁ ለመመዘን DEEL ከዲስትሪክቱ ጋር በትብብር ይሰራል። በ DEEL የቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤት ፕሮግራሞች ውስጥ የተመዘገቡ ልጆች በዲስትሪክቱ ውስጥ የሚኖራቸው የK-12 የትምህርት ቆይታ አፈጻጸም ላይ በሚደረግ ክትትል የፕሮግራሙን የረጅም ጊዜ ውጤታማነት መለካት እንዲቻል ዲስትሪክቱ ለልጆቹ የተማሪ መታወቂያ ቁጥሮችን ያዘጋጃል። DEEL የዲስትሪክት ተማሪ መታወቂያ ቁጥሮችን ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ በቂ መረጃዎችን ደኅንነቱ በተጠበቀ የፋይል ማስተላለፊያ ዘዴ ለዲስትሪክቱ ሊያቀርብ ይችላል።

DEEL በማስተማር ስልቶቻቸው ዙሪያ የሚያተኩር በማስረጃ የተደገፈ ስልጠና እና ግምገማዎችን ለመምህራን ያቀርባል። አልፎ አልፎ በመምህራን ክትትል ወቅት ልጅዎ ፎቶ ሊነሳ ወይም ቪዲዮ ሊቀረጽ ይችላል። የማንኛውም ቀረጻ ዋና ትኩረት መምህሩ ላይ ሲሆን፣ ቀረጻዎቹን ማየት የሚችሉት የDEEL/SPP ሰራተኞች ወይም የውጭ ገምጋሚዎች ብቻ ናቸው። የልጅዎን ግላዊ መረጃ ለመጠበቅ ሲባል ሁሉም የተቀረጹ ምስሎች በሚስጥር ተይዘው የሚቆዩ ሲሆን፣ በሁለት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ እንዲሰረዙ ይደረጋል።*

Public Health (የሕዝብ ጤና ጥበቃ መሥሪያ ቤት) የጥራት ደረጃዎች በመጠበቅ እና ይፋዊ መመሪያ በመስጠት ረገድ ለትምህርት ክፍሎች ድጋፍ ይሰጣል። አልፎ አልፎ Public Health ምልከታ በሚያደርግበት ወቅት የልጅዎ ፎቶ ወይም ቪዲዮ ሊቀረጽ ይችላል። ማንኛውም የተቀረጸ ምስል ዋና ትኩረቱ የትምህርት ክፍሉ ሁኔታ ላይ ሲሆን፣ ቅጂውን ማየት የሚችሉትም የ public health አጋሮች ብቻ ናቸው። የልጅዎን ግላዊ መረጃ ለመጠበቅ ሲባል ሁሉም የተቀረጹ ምስሎች በሚስጥር ተይዘው የሚቆዩ ሲሆን፣ በሁለት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ እንዲሰረዙ ይደረጋል።*

DEEL የቤተሰቦችን እና የልጆችን መረጃ በከተማ አስተዳደሩ የግላዊ መረጃ ጥበቃ ስታንዳርዶች (City's Privacy Standards) መሠረት በጥንቃቄ ይጠብቃል። በሕግ የሚፈለግ ሆኖ በሚገኝባቸው የተወሰኑ አጋጣሚዎች ላይ መረጃዎች ለሕዝብ ይፋ ሊሆኑ ይችላሉ። DEEL በፕሮግራሞቻችን ውስጥ የተመዘገቡ ልጆችን ወይም የቤተሰብ አባላቶቻቸውን/የአሳዳጊዎቻቸውን ማንነት ሊገልጹ የሚችሉ የግል መረጃዎችን አሳልፎ አይሰጥም። ለተጨማሪ መረጃ እባክዎን የግላዊነት መግለጫውን ይመልከቱ።

ስላገኙት ተሞክሮ አስተያየትዎን ለመጠየቅ DEEL በቀጥታ ወይም በአገልግሎት አቅራቢዎ በኩል ሊያነጋግርዎት ይችላል።

## የግላዊነት መግለጫ

የሚሰጡት መረጃ ጥቅም ላይ የሚውለው ማመልከቻዎን ለመገምገም ነው። ብቁ ሊሆኑ የሚችሉባቸው ሌሎች ተጨማሪ ፕሮግራሞችን የሚመለከት መረጃ ለእርስዎ ለማቅረብ ሲባል፣ የሲያትል ከተማ አስተዳደር እርስዎ የሰጡትን መረጃ ለሲያትል ከተማ አስተዳደር መምሪያዎች ሊያጋራ ይችላል። እርስዎ ብቁ በሆኑበት ተጨማሪ ፕሮግራም ውስጥ ለመመዝገብ ፈቃድዎን ከሰጡ፣ የሲያትል ከተማ አስተዳደር በዚያ ተጨማሪ ፕሮግራም ምዝገባዎን ለማከናወን መረጃውን ለሲያትል ከተማ አስተዳደር መምሪያዎች ሊያጋራ ይችላል። ሕግ ካላስገደደን በስተቀር፣ መረጃዎን ለማንኛውም ዓይነት የሕግ ማስከበር ተግባርም ሆነ ለሌላ ዓላማ እያወቅን አሳልፈን አንሰጥም። ለበለጠ መረጃ፣ እባክዎን Public Records Act (የሕዝብ መዝገቦች አዋጅ) - RCW ምዕራፍ 42.56ን ይመልከቱ። የሲያትል ከተማ አስተዳደር የግላዊነት መግለጫ እርስዎ የሚሰጡንን መረጃዎች እንዴት እንደምናስተናግድ ያብራራል።

*የDEEL/የሲያትል ከተማ አስተዳደር በPublic Records Act (PRA) የሚመራ ኤጀንሲ እንደመሆኑ ቀደም ብሎ የተጠቀሰው የDEELን የአሠራር ፖሊሲ እና የታቀደ እንቅስቃሴ የሚወክል ቢሆንም፣ DEEL ሊገኙ የሚችሉ ማናቸውም ልዩ ሁኔታዎች ወይም ተቃውሞዎችን የማቅረብ መብቱን እያስጠበቀ መዝገቦች እንዲጠበቁ ወይም እንዲለቀቁ ለሚጠይቁ ማናቸውም ሕጋዊ ግዴታዎች ተገዥ ይሆናል።

የልጁ የመጀመሪያ/የመጨረሻ ስም:- ______________________________ የልጁ የትውልድ ቀን:- ____________________

## አማራጭ ፈቃዶች

በቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤት ፕሮግራሙ ውስጥ በመሳተፍ፣ ወላጆች/ሕጋዊ አሳዳጊዎች ከላይ በተጠቀሱት ነጥቦች በሙሉ መስማማታቸውን ያረጋግጣሉ። የሚከተሉት በፍላጎት መሠረት የሚሰጡ አማራጭ ፈቃዶች ናቸው።

ለሚስማሙበት እያንዳንዱ አማራጭ ፈቃድ ለመስጠት አጠገቡ ባለው ሳጥን ላይ ምልክት ያድርጉ።

- ☐ የፕሮግራም ግምገማ:- DEEL የክፍል ውስጥ ትምህርት ጥራት በልጆች የመማር ሂደት ላይ ያለውን ተጽዕኖ ለመገምገም ከውጭ ገምጋሚዎች ጋር ውል ተዋውሎ ሊሠራ ይችላል። የውጭ ተመራማሪዎች በልጆች የቋንቋ ችሎታ፣ የማንበብ እና የመጻፍ ክህሎት፣ የሒሳብ ችሎታ እና ልጆችን ለመማር የሚረዱ ባህሪያት ዙሪያ ለልጆች ተስማሚ የሆኑ ምዘናዎችን ሊያካሂዱ ይችላሉ። ይህንን ፈቃድ በማንኛውም ጊዜ መሰረዝ ይችላሉ። ልጄ ለፕሮግራም ግምገማ በልጆች ደረጃ በሚዘጋጁ ምዘናዎች ላይ እንዲሳተፍ ፈቃዴን ሰጥቻለሁ።

- ☐ የመመዝገቢያ ሰነዶችን ማጋራት:- የቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤትዎ ወይም የልጅ እንክብካቤ አገልግሎት አቅራቢዎ ለአስተዳደራዊ ዓላማዎች ሰነዶችን እንዲያቀርቡ ሊጠይቅዎት ይችላል። ለእርስዎ ምቾት ሲባል DEEL ለከተማ አስተዳደሩ ያስገቧቸውን ሰነዶች ለአገልግሎት አቅራቢዎ ሊያጋራ ይችላል። DEEL የዕድሜ ማረጋገጫ፣ አድራሻ ወይም የገቢ ሰነዶችን ለአገልግሎት አቅራቢዬ እንዲያጋራ ፈቃዴን ሰጥቻለሁ።

- ☐ የፎቶ/ቪዲዮ ፈቃድ:- የልጄ ፎቶ ወይም ቪዲዮ ለማስተዋወቂያ ዓላማዎች እንዲቀረጽ ፈቃዴን ሰጥቻለሁ:- ከከተማ አስተዳደሩ የቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤት ፕሮግራሞች ጋር ለተያያዘ ዲጂታል ይዘት፣ ሕትመት እና ቪዲዮ (ይህ ፈቃድ በቋሚነት የሚያገለግል ነው)።

ከ DEEL ጋር የሚደረግ ግንኙነት:- የምዝገባ ሂደቱ በሚከናወንበት ወቅት እንዲሁም አልፎ አልፎ በሚነሱ ከምዝገባ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ዙሪያ DEEL ሊያነጋግርዎት ይችላል። ለሌሎች ጉዳዮች እንዲያነጋግሩዎት ከፈለጉ፣ እባክዎን ከታች ያሉት ሳጥኖች ውስጥ ምልክት ያድርጉ።

- ☐ በ DEEL ወይም በሌሎች የከተማ አስተዳደሩ መምሪያዎች በሚዘጋጁ ቃለ መጠይቆች ወይም የገንዘብ ድጋፍ ፓናሎች ላይ የሚደረግ ተሳትፎን በተመለከተ።
- ☐ ከDepartment of Education and Early Learning ወቅታዊ መረጃዎችን በኢሜይል ማግኘትን በተመለከተ።
- ☐ የቃለ-መጠይቅ ዕድሎች፣ አጭር አስተያየቶች ወይም መረጃ መስጠትን አስመልክቶ።

ከላይ የሰጧቸውን ማናቸውንም ፈቃዶች በማንኛውም ጊዜ መሰረዝ ከፈለጉ፣ እባክዎን በቀጥታ DEELን በpreschool@seattle.gov ወይም The Seattle Preschool Program, PO Box 94665, Seattle, WA 98124 በኩል በጽሑፍ ያሳውቁ። ይህ ፈቃድ የትኛውም ይቅደም አዲስ የተሻሻለ ፈቃድ እስከሚቀርብ ድረስ ወይም እስከ 8/31/2027 ድረስ ተፈጻሚ ሆኖ ይቆያል።

## አስፈላጊ የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ

ከታች ፊርማዬን በማስቀመጥ እኔ **1)** ልጄ በDEEL የቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤት ፕሮግራም ውስጥ እንዲሳተፍ ፈቃዴን እሰጣለሁ፣ **2)** የግላዊነት መግለጫውን ማንበቤን አረጋግጣለሁ፣ እንዲሁም **3)** ከላይ በተጠቀሰው መሠረት መረጃ እንዲጋራ ፈቃድ እሰጣለሁ። ብቁ መሆን አለመሆኔን ለመወሰን የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ሙሉ በሙሉ አለመስጠት እና/ወይም የሐሰት ሰነዶች ማቅረብን ጨምሮ ሐሰተኛ መረጃ ሰጥቼ ከተገኘሁ በፕሮግራሙ ከማደርገው ተሳትፎ ልሰረዝ እንደምችል እገነዘባለሁ።

| | |
|---|---|
| የወላጅ/የሕጋዊ አሳዳጊ ፊርማ:- | |
| የወላጅ/ሕጋዊ አሳዳጊ ስም በግልጽ ጽሑፍ:- | |
| ቀን:- | |

Seattle Department of Education & Early Learning

SEATTLE PRESCHOOL PROGRAM

CCAP CHILD CARE ASSISTANCE PROGRAM

# ለማረጋገጫ ተቀባይነት ያላቸው ሰነዶች

እባክዎ ይህንን መረጃ ለሲያትል የትምህርት እና የቅድመ ትምህርት ክፍል (DEEL) መዋዕለ ሕፃናት እና የሕፃናት እንክብካቤ ፕሮግራሞች የልጅ ዕድሜ፣ የቤተሰብ አድራሻ እና ገቢን ለማረጋገጥ የተቀበሉትን ሰነዶች ዓይነት እና ቅርፀት ለመለየት ይጠቀሙበት። ሥዕሎች ወይም የኤሌክትሮኒክስ የሰነዶች ሥሪቶች ተቀባይነት አላቸው።

## የልጅ ዕድሜ

የፕሮግራሞችን የዕድሜ መስፈርት ለማረጋገጥ፣ ከዚህ ዝርዝር ውስጥ የልጁን ስም እና የትውልድ ቀን የያዘ አንድ ሰነድ ያስገቡ፦

- የልደት የምስክር ወረቀት
- የሕክምና መዝገብ
- የኢሚግሬሽን ሰነድ
- ፓስፖርት
- በመንግስት የተሰጠ መታወቂያ

## አድራሻ

ለትምህርት እና የቅድመ ትምህርት ክፍል (DEEL) ፕሮግራሞች ብቁ ለመሆን ቤተሰቦች በሲያትል ውስጥ መኖር አለባቸው። በሽግግር ላይ ላሉ ቤተሰቦች፣ ቤት እጦት ላጋጠማቸው፣ ወይም በሌላ መልኩ የአድራሻ ሰነዶችን ማቅረብ ለማይችሉ፣ እዚህ የሚገኘውን የመኖሪያ ቅጻችንን ይጠቀሙ። ሁሉም ሰነዶች የወላጅ/አሳዳጊን ሙሉ ስም ማካተት እና ባለፉት ሦስት ወራት ውስጥ ቀኑ የተፃፈ ወይም የቅርብ ጊዜ እንደሆነ የሚታወቅ መሆን አለበት። ከፖስታ ውጫዊ ክፍል ያለ መረጃ ተቀባይነት የለውም። አንድ ዋና ሰነድ ወይም ሁለት አማራጭ ሰነዶችን ያቅርቡ።

### የዋና አድራሻ ማረጋገጫዎች

ከዚህ ዝርዝር አንድ ሰነድ ያስገቡ፦

- የፍጆታ ክፍያ
  - ለምሳሌ ጋዝ፣ ውሃ/ቆሻሻ፣ በይነመረብ፣ መብራት/ኤሌክትሪክ፣ ኬብል፣ መደበኛ ስልክ፣ ወዘተ።
- የቤት/የተከራይ መድህን
- የቤት ግዢ ሕጋዊ ሰነድ
- የተፈረመ የኪራይ ውል
- የቤቶች ኤጀንሲ ደብዳቤ
- የኪራይ ደረሰኝ

### አማራጭ የአድራሻ ማረጋገጫዎች

ከዚህ ዝርዝር ውስጥ ከተለያዩ ምንጮች ሁለት ሰነዶችን ያስገቡ፦

- የመድህን ሰነዶች
  - ምሳሌዎች ጤና፣ መኪና፣ ኪራይ፣ ወዘተ ያካትታሉ።
- የገንዘብ ሰነዶች
  - ለምሳሌ የባንክ መግለጫ፣ የክሬዲት ካርድ መግለጫ፣ የተማሪ ብድር መግለጫ፣ ወዘተ።
- የገቢ ሰነዶች
  - ምሳሌዎች TANF፣ SSI፣ paystub፣ ወዘተ ያካትታሉ።
- የመንጃ ፈቃድ
  - ወቅታዊ መሆን አለበት
- ሌሎች የክፍያ ሒሳቦች

## ገቢ

በቤተሰብዎ ውስጥ ወላጅ/አሳዳጊ(ዎች) ለሚቀበሉት ገቢ ሁሉ ሰነድ ያስገቡ። የሚፈለገው ሰነድ በገቢ ምንጩ ላይ የተመሰረተ ነው። በሲያትል የቅድመ ትምህርት ቤት ፕሮግራም (SPP) ውስጥ እየተመዘገቡ እና የSNAP ወይም የTANF ጥቅማ ጥቅሞችን እየተቀበሉ ከሆነ፣ የአሁኑን የጥቅማ ጥቅሞች ማረጋገጫ ያስገቡ ወይም እዚህ የሚገኘውን የDSHS የስምምነት ቅጽ ይፈርሙ። ተጨማሪ የገቢ ማረጋገጫ አያስፈልግም። በሲያትል የቅድመ ትምህርት ቤት ፕሮግራም ውስጥ የተመዘገቡ እና ሙሉ የትምህርት ክፍያ ለመቀበል ፈቃደኛ የሆኑ ቤተሰቦች የገቢ ሰነዶችን ማቅረብ አያስፈልጋቸውም፣ ይልቁንስ እዚህ የሚገኘውን የሙሉ የትምህርት ክፍያ ቅጽ ይሙሉ።

### ሥራ

- በጣም የቅርብ ጊዜ የሦስት ወራት ሙሉ የደመወዝ ክፍያ ደረሰኞች ቀሪ
  - ደመወዝ በየሳምንቱ ነው የሚከፈልዎት? 12 የደመወዝ ክፍያ ደረሰኞች ቀሪ
  - በየሁለት ሳምንቱ ይከፈላሉ? ከ5 እስከ 7 የደመወዝ ክፍያ ደረሰኞች ቀሪ
  - በወር ሁለት ጊዜ ይከፈላሉ? 6 የክፍያ ደረሰኞች ቀሪ
  - በየወሩ ይከፈላሉ? 3 የደመወዝ ክፍያ ደረሰኞች ቀሪ
- የአሰሪ ደብዳቤ ወይም ኢሜይል
  - ያለፉት 3 ወራት የክፍያ ወረቀቶች በማይገኙበት ጊዜ። ካለፉት 90 ቀናት ጀምሮ የሚጀምርበትን ቀን፣ የሰሩትን ሰዓታት፣ ደመወዝ፣ እና ቀኑን ያካትቱ
- የራስ ሥራ
  - እዚህ የሚገኘውን የራስ ሥራ ቅጽ ይጠቀሙ

### የልጅ ድጋፍ


- በፍርድ ቤት የታዘዘ
  - መጠንን የሚገልጽ ይፋዊ ሰነድ
- ሌላ
  - እዚህ የሚገኘውን የልጅ ድጋፍ ቅጽ ይጠቀሙ

### ተማሪ

- የገንዘብ እርዳታ
  - የሽልማት ደብዳቤ እና የትምህርት ክፍያ መግለጫ
- የሥራ ጥናት
  - የሽልማት ደብዳቤ ወይም የተቆጣጣሪ ደብዳቤ ከሰዓታት/ደመወዝ ጋር

### ሌላ ገቢ

- ኣነስተኛ ገቢ ላላቸው ከመንግስት የሚሰጥ የጥሬ ገንዘብ ጥቅማጥቅሞች
  - የአሁኑ የሽልማት ደብዳቤ (TANF፣ SSI ወይም ሌሎች የገንዘብ ጥቅማ ጥቅሞች) ወይም እዚህ የሚገኘውን የDSHS የስምምነት ቅጽ ይፈርሙ
- ሌላ ገቢ
  - የሦስት ወር መግለጫ
- የኪራይ ገቢ
  - የቅርቡ የግብር ዓመት የግብር ሰነድ «Schedule E»





## ደረጃ 3፡- ለ Department of Education & Early Learning (DEEL) ወይም ለአቅራቢው ያስገቡ

ይህን የተሞላ የምዝገባ ጥቅል ከሰነዶችዎ ጋር በተቻለ ፍጥነት ተመላሽ ያድርጉ።
ሙሉ ጥቅልዎ ከሰነዶች ጋር በፍጥነት ለእኛ ከደረሰ በፍጥነት ለማከናወን ያስችላል።

ተጨማሪ ሰነድ ካስፈለገ፣ የ DEEL የመረጃ ቡድን ወይም አቅራቢዎ ሊያነጋግሩዎ ይችላሉ።

እገዛ ካስፈለገዎት፣ እባክዎ በስልክ ቁጥር (206) 386-1050 ይደውሉ ወይም ኢሜይል ያድርጉ preschool@seattle.gov




## ደረጃ 4፡- የምዝገባ ማረጋገጫ ይቀበሉ

የመረጃዎ ትክክለኛነት አንዴ ከተረጋገጠ፣ ልጅዎ በቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ውስጥ በይፋ ስለመመዝገቡና መክፈል ስለሚገባዎ የትምህርት ክፍያ ማሳወቂያ ይደርስዎታል። የ SPP ክፍያዎን ለመገመት፣ የክፍያ ማስያውን ለመጠቀም www.seattle.gov/applyspp ይጎብኙ።
የቀረበው መረጃ እርስዎ ለፕሮግራሙ ብቁ አለመሆንዎትን ካረጋገጠ፣ DEEL ወይም አቅራቢዎ ይህንኑ ያሳውቅዎታል።

የልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎ ለምዝገባው ሒደት ተጨማሪ ሰነዶች መሟላት ያለባቸው እንደሆነ እስከሚያረጋግጥ ድረስ **ልጅዎ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ላይጀምር ይችላል።**